# የህግ ጥሰት በሚኒስትሩ አንደበት

እሁድ ጥር 24 ቀን 2001 ዓ.ም. ለንባብ የበቃው ሪፖርተር ጋዜጣ የፍትህ ሚኒስትር ብርሃነ ሀይሉን አነጋግሮ ከአንደበታቸው የወሰደውን ቃል አስፍሮ ያስነበበው ዜና ወቅታዊና ተፈላጊ እንዲሁም የጋዜጠኝነትን ሥነ-ምግባር የተከተለ አሠራር በመሆኑ አዘጋጆቹን ሊያስመሰግናቸው ይገባል፡፡

ሆኖም ግን የጋዜጠኛነት ሞያ ባለሥልጣናት ሊናገሩ የሚፈልጉትን ብቻ አዳምጦ መጻፍን ሳይሆን ሊናገሩ የሚገባቸውንና እነርሱ መናገር የማይፈልጉትን አንባቢ ግን ሊያውቀው የሚገባን ጉዳይ ከተለያየ አቅጣጫ በመጠየቅ እውነትን መፃፍ የሚጠይቅ ሙያ ነው፡፡

በመሆኑም ሪፖርተር ጋዜጣ 18 ወራት የፈጀውን የሽምግልና ሂደት ጠቅሶና ሽማግሌዎቹ በወቅቱ የሰጡትን መግለጫ አስታውሶ ሚኒስትር ብርሃነ ሀይሉ የሚሉትን ቢያቅርብ ዜናውን የተዋጣለትና የተሟላ ያደርገው ነበር፡፡

ይህም ሆኖ በቀረበው መልኩ ሁለት መሠረታዊ የህግ ጥሰቶችን አንባቢ ከራሳቸው ከፍትህ ሚኒስትሩ እንዲረዳ ያስቻለ ወቅታዊ ዜና ነው፡፡ ወ/ት ብርቱካን ለሪፖርተር ጋዜጣ በላኩት ቃሌ በሚል ፅሑፋቸው ይቅርታ መጠየቄን አልካድኩም የሚል ምላሽ ሰጥተው ነበር፡፡ ይህ እንደማስተባበያ አይቆጠርም ወይ በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ አቶ ብርሃነ ሲመልሱ፡- «ፖሊስ ጋር ሄደው የገለፁት ነገር የለም፡፡ ማስተባበያ እንዲሰጡ ጥያቄ ያቀረበው ህጋዊ የመንግሥት አካል ፖሊስ ነው፡፡ እንዲያስተባብሉ ጥሪ ቢደረግላቸው ያሳወቁት ነገር የለም፡፡» ማለታቸውን ከሪፖርተር አንብበናል፡፡

አቶ ብርሃነ ይህን የተናገሩት ድርጊቱ ከተፈፀመ አንድ ወር ካለፈውና ፖሊስ ጠርቶ መጠየቁና በመገናኛ ብዙሀን ማሰጠንቀቂያ መስጠቱ ምንም የህግ መሠረት የሌለው ተግባር  ንደሆነ በተለያየ መንገድ ከተገለፀ በኋላ መሆኑ በጣሙን አስገርሞናል፡፡

ድርጊቱ በተፈፀመበት ወቅት አዋጁን ለማየት ትዕግስትም ጊዜም ታጥቶ ሊሆን ይችላል፡፡ ከዛ በኋላ ግን አዋጁን መለስ ብሎ ለማየት ረዥም ቀናት አልፈዋል፡፡ የሚነገረው ግን ዛሬም የትናንቱን ስህተት የሚያጠናክር እንጂ ስህተትን መለስ ብሎ አይቶ የሚያስተካክል አይደለም፡፡ ይህ ደግሞ ህጉ ተግባራዊ የሚሆነው ህገ-መንግሥቱ ላይ በተፃፈውና አዋጆችም ላይ በሠፈረው መልኩ ሳይሆን ባለሥልጣኖች በሚፈልጉት መንገድ ነው እንድንል ያስገድደናል፡፡

እኛም እንደ አቶ ብርሃነ ህጉን ወደ ጐን አድርገን እነርሱ በያዙት መንገድ ክርክሩን እናስኪደው ብንል «ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በመገናኛ ብዙሃን ለተጠየቁት ጥያቄ በሚያስተናግዷቸው መገናኛ ብዙሃን ምላሽ ሰጥተዋል» ማለት ይቻላል፡፡ ፍሬ ነገሩ ግን ይህ አይደለም፡፡ ከማነጋገር አልፎ አከራካሪ የሚሆነው ዋናው ጉዳይ ምንም አሻሚ ትርጉም የሌለው ግልፅና በቀጥታ ተፈፃሚ መሆን የነበረበት አዋጅ ቁጥር 395/96 አንቀጽ 4(3) ተግባራዊ ያለመሆኑ ነው፡፡ አንቀጽ 4(3) «ፕሬዝዳንቱ በቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ይቅርታ የሚሰጣቸው ሰዎች ቅድመ ሁኔታውን ካላሟሉም ወይም ጥሰዋል የሚል ክስ

ሲቀርብባቸው ጉዳዩን መርምሮ ለፕሬዝዳንቱ የውሳኔ ሀሳብ ያቅርባል» በማለት ስልጣን የሰጠው ለይቅርታ ቦርድ ነው፡፡ አቶ ብርሃነ ሀይሉ ወ/ት ብርቱካን ፖሊስ ዘንድ ቀርበው ማስተባበል ነበረባቸው ሲሉ የተናገሩትን ከዚህ የአዋጅ ቁጥር 395/96 አንቀጽ 4(3) ድንጋጌ ጋር  እንደምን ሊያስማሙት ይቻላቸዋል? እንደ አዋጁ አንቀጽ 4(3) እና 10(2) ድንጋጌ በይቅርታ ማንሳት ጉዳይ ስልጣን ያላቸው ይቅርታ ቦርድና ፕሬዝዳንቱ ናቸው፡፡ በወ/ት ብርቱካን መታሠር ጉዳይ ግን ዋንኛ ተዋናይ የሆኑት ፖሊስና ፍትህ ሚኒስትር ናቸው፡፡ ነገሩን ግራ ያደረገውና የህግ ጥሰቱን በይፋ ያጋለጠው አንዱ ይህ ነው፡፡

ሪፖርተር ያነሳው ሁለተኛው ጉዳይ በጣም መሠረታዊ የሆነውንና ወ/ት ብርቱካንን ለእስር ባበቁት ወገኖች በግልፅ የተጣሰውን የአዋጅ አንቀጽ 17(2) የሚመለከት ነው፡፡ ወ/ት ብርቱካን የ20 ቀን ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባ ነበር በሚል ለሚነሳው ጥያቄም አቶ ብርሃነ  ሀይሉ ሲመልሱ «አንቀጾችን ለያይቶ የመመልከት ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር የግድ ሃያ ቀን አያስፈልግም ብለዋል፡፡» በማለት ነው ጋዜጣው የገለፀው፡፡

ሚኒስትር ብርሃነ ሀይሉ አዋጅ ላይ የሠፈሩት አንቀጾች ተደራርበው ይሁን ተለያይተው «የግድ ሃያ ቀን እንደማያስፈልግ» የሚደነግጉበትን ሁኔታ ቢያብራሩ ተገቢ ይሆን ነበር፡፡ በመሠረቱ አንድ አዋጅ የሚይዛቸው አንቀጾች ተደጋጋፊና አንደኛው አንቀጽ የሌላኛውን መኖር ግድ የሚሉ እንጂ ለየብቻቸው የሚቆሙ ወይንም በተናጠል እየተመዘዙ የሚተረጐሙ አይሆኑም፡፡

አዋጅ 395/96 አንቀጽ 17 ይቅርታን ለማንሳት መሟላት ያለባቸው ጉዳዮች በማለት በሁለት ንዑሳን አንቀጾች የገለፃቸው ጉዳዮች የሚሽር ወይንም ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ ባልሆነበት ሁኔታ ይቅርታን ለማንሳት የሚያስችል ክፍተት የሚሰጥ አንቀጽ ፈፅሞ የለም ሊኖርም አይችልም፡፡

አንቀጽ 17(1) «ይቅርታ ለማሠረዝ የሚያበቃ በቂ ምክንያት ከተገኘ ምክንያቱ በግልፅና ይቅር የተደረገለት ሰው በሚገባው ቋንቋ በፅሑፍ ተዘጋጅቶ ለይቅር ተባዩ እንዲደርሰው ይደረጋል፡፡» ይላል፡፡

አንቀጽ 17(2) ደግሞ «ደብዳቤው የደረሰው ሰው ምላሽ ለመስጠት ከ20 ቀን ያላነሠ ጊዜ የማግኘት ዕድል እንዳለው ይደነግጋል፡፡ ይህን ደፍጥጦ ለማለፍ የሚያበቃ የህግ መሠረት የለም፡፡ ተፈፃሚ ላለማድረግም ሊቀርብ የሚችል አንዳችም ምክንያት የለም፡፡ ለህግ የበላይነት አለመገዛት ካልሆነ በስተቀር የህግ የበላይነት መከበር በግለሰቦች መልካም ፈቃድና ፍላጐት ላይ ሳይሆን በህገ-መንግሥቱና ሱን መሠረት አድርገው በሚወጡ አዋጆች ላይ ተመስርቶ ተግባራዊ የሚሆን ነው፡፡ በግልፅ የተፃፈን አዋጅ  የጣሱ ለህግ የበላይነት መከበር የተፈፀመ ነው ማለት ዛሬ ባይሆን ነገ ያስጠይቃል፡፡